1354 ለእኝ

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፑብሊክ
የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA
ETHIOPIAN REVENUES AND CUSTOMS AUTHORITY

ቁጥር / Ref. No S.0/2553/08
ቀን / Date 15 መስከረም 2008

በአባሪው ለተዘረዘሩት በሙሉ

**በያሉበት**

ጉዳዩ፡- <u>በህገ ወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት አስተዳደርና አወጋገድ ማንዋል ይመለከታል</u>

የቁም እንስሳትን ግብይት ዘመናዊ ፍትሀዊና ተወዳዳሪ በማድረግ አርቢው የግብይት ተዋናይና ተጠቃሚ ለማድረግ ታስቦ በፌዴራል የንግድ ሚኒስቴር የተዘጋጀ የተያዙ የቁም እንስሳትን አስተዳደርና አወጋገድ አሰራር ማንዋል ከዚህ ሽኚ ደብዳቤ ጋር የላክን መሆኑን እየገለፅን በዚሁ መሰረት እንዲፈፀም እናሳስባለን፡፡

ከሠላምታ ጋር
አለማየሁ ንጉሴ
ምክትል ዋና ዳይሬክተር
(የኦፕሬሽን ማስከበር ዘርፍ)

**ግልባጭ፡-**

- ለዋና ዳይሬክተር ጽ/ቤት
- ለጉምሩክ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ሥራዎች ዘርፍ
- ለአገር ውስጥ ታክስ ፕሮግራም ልማትና ድጋፍ ስራዎች ዘርፍ
- አዲስ አበባ ቅ/ጽ/ቤቶች ድጋፍና ክትትል ዳይሬክቶሬት

<u>ኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን</u>

✓ አዲስ አበባ ቃሊቲ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዲስ አበባ</u>

✓ መቀሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>መቀሌ</u>

✓ ለአዳማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
<u>አዳማ</u>



ስልክ ቁ / Tel.. 011 662 98 00
ፋክስ / Fax: 011 662 99 06
ኢሜል / Email: erca@ethionet .et
ድረ ገጽ / Website: www.erca.gov.et
ፖ.ሣ.ቁ / P.O.Box: 2559
አዲስ አበባ -ኢትዮጵያ
Addis Ababa, Ethiopia

- ✓ ለሚሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሚሌ
- ✓ ለባህርዳር ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ባህርዳር
- ✓ ለጅጅጋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅጅጋ
- ✓ ለድሬዳዋ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ድሬዳዋ
- ✓ ለኮምቦልቻ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ኮምቦልቻ
- ✓ ለሞያሌ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞያሌ
- ✓ ለሐዋሳ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሐዋሳ
- ✓ ለጅማ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጅማ
- ✓ ለሞጆ ገቢዎችና ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ሞጆ
- ✓ ጋላፊ ጉምሩክ ቅ/ጽ/ቤት
  ጋላፊ
  በያሉበት

ፑ/ሶ 38 2/12/07 ጋ/ጄ/ር ጀ/ዋ ... 1/12/07 ህመ 3056 4/12/07

29 ሐምሌ 2007
01-85/564

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የንግድ ሚኒስቴር

The Federal Democratic Republic of Ethiopia
Ministry of Trade

ለ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን

አዲስ አበባ

ጉዳዩ፦ በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት አስተዳደር እና አወጋገድ ማንዋል ይመለከታል

የቁም እንስሳት ግብይትን ዘመናዊ ፤ፍትሀዊና ተወዳዳሪ በማድረግ አርቢውን ፤ህጋዊ የግብይት ተዋንያን፤ ሸማቾቹ እና ሀገሪቱ ከግብይቱ ተገቢውን ጥቅም እንዲያገኙ ለማስቻል የቁም እንስሳት ግብይት የሕግ ማዕቀፎች ማለትም የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ ቁጥር 819/2006 ፤ደንብ ቁጥር 341/2007 እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 004/2007 ጸድቀው በስራ ላይ መዋላቸው ይታወቃል፡፡

ሆኖም በተለያዩ ጊዜያት በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች በተደረገ የመስክ ምልከታና ግምገማዎች የግብይት ስርዓት ዝርጋታውን በተሟላ መልኩ መሬት በማውረድ ህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድን በመከላከል ረገድ ውስንነቶች የነበሩ መሆኑ ለማየት ተችሏል፡፡

ለዚህም በዋናነት በክልሎች እና ከተማ አስተዳደሮች መከናወን የሚገባቸው ተግባራት በሚፈለገው ፍጥነት ያለመከናወናቸው መሆኑን መግባባት ላይ የተደረሰ ሲሆን በፌዴራል በኩል ህገወጥ ግብይት የተፈጸመባቸው እና በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት አስተዳደር እና አወጋገድ በተመለከተ ወጥ ማንዋል መዘጋጀት እንደሚገባው መግባቢያ ላይ ተደርሷል፡፡

በዚህም መሰረት ማንዋሉን በማዘጋጀት እና በፌዴራል ኮማንድ ፖስት አባላት አስተያየት እንዲሰጥበት በማደረግ እንዲዳብር የተደረገ ሲሆን ማንዋሉ የተያዙ የቁም እንስሳትን አስተዳደርና አወጋገድ ሒደት ቀላልና ግልፅ ለማድረግ ያስችላል ፡፡

በመሆኑም ማንዋሉን ከማስፈፀም አንጻር ለሚመለከታቸው ተቋማት እስከታችኛው መዋቅር ድረስ እንዲደርስ እና እንዲፈጸም እንዲደረግ እየገለፅን ማንዋሉን ከዚህ ሸኚ ደብዳቤ ጋር አባሪ አድርገን የላክን መሆኑን እንገልፃለን፡፡

ከሠላምታ ጋር

ያዕቆብ ያላ
ሚኒስትር ዴኤታ

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

እንዲያውቁት
ለክቡር ሚኒስቴር ፅ/ቤት
ንግድ ሚኒስቴር

☎ 251-11-551 80 25-29 Fax 251-11-551 54 11 553 10 27, 552 24 19
✉ 704
አዲስ አበባ - ኢትዮጵያ
Addis Ababa Ethiopia

# በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

## የንግድ ሚኒስቴር

# ህገወጥ ግብይት የተፈጸመባቸው እና

# በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳት አያያዝ፣ አስተዳደር እና አወጋገድ /የሽያጭ ሂደት/ ስርዓት ማንዋል

ሀምሌ 2007

<u>አዲስ አበባ</u>

ማውጫ


መግቢያ .......... 2
ዓላማ .......... 3
**ክፍል አንድ** .......... 3
1.በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳት ማቆያ .......... 3
2.ህገወጥ የቁም እንስሳት አያያዝና ርክክብ ስርዓት .......... 4
**ክፍል ሁለት** .......... 6
3.በህገወጥ ዝውውርና ኮንትሮባንድ ንግድ የሚያዙ የቁም እንስሳት አስተዳደር .......... 6
ሀ. ቋሚ የእንስሳት ማቆያ ጣቢያዎች አስተዳደር .......... 7
ለ. ጊዜያዊ የቁም እንስሳት ማቆያ ጣቢያዎች /የዩኒየን፣ ግለሰብ ማድለቢያ፣ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል እና ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎች/ አስተዳደር .... 8
**ክፍል ሶስት** .......... 11
4.አወጋገድ/ሽያጭ ሂደት .......... 11
5.የሽያጭ ገንዘብ አስተዳደር .......... 14
**ክፍል አራት** .......... 15
6.በጊዚያዊ የቁም እንስሳት ማቆያ የሚሞቱ እንስሳትን በተመለከተ .......... 15
7.ህገወጥ የቁም እንስሳትን የጫኑ ተሽከርካሪ፤አሽከርካሪ እና የቁም እንስሳት ባለቤት በተመለከተ .......... 16
9.የክትትልና የግምገማ ስርዓት .......... 16
10.የተለያዩ ቅፃቅፆች .......... 18



ንግድ ሚኒስቴር
Ministry of Trade
Archives
መዝገብ ቤት



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

## መግቢያ

ኢትዮጵያ በዓለም ላይ በእንስሳት ሀብታቸው ብዛትና ለእንስሳት እርባታ አመቺነት ቀዳሚውን ሥፍራ ከሚይዙት አገሮች ተርታ እንደምትመደብ መረጃዎች ያመለክታሉ፡፡ በማዕከላዊ ስታስቲክስ ኤጀንሲ እ.ኤ.አ 2009 የቀረበ ጥናት እንደሚያመለክተው አገሪቱ 52 ሚሊዮን የዳልጋ ከብት, 2 ነጥብ 5 ሚሊዮን ግመል, 33 ሚሊዮን በግ እና 30 ሚሊዮን ፍየል አላት፡፡ ይሁን እንጂ በተለያዩ ችግሮች ምክንያት ከንዑስ ዘርፉ እያገኘች ያለችው ጥቅም ከሚጠበቀው አንጻር እጅጉን ያነሰ ነው፡፡

ለዚህም ዋና ዋና ምክንያቶች የሆኑት የእንስሳት እርባታ ስርዓታችን ኋላ ቀርና ገበያ መር አለመሆኑ፣ ዘመናዊ የቁም እንስሳት የግብይት ሥርዓት ተዘርግቶለት የሚመራ ካለመሆኑ ጋር ተያይዞ የህገወጥ የቁም እንስሳት ንግድ መስፋፋት፣ የእንስሳት ጤና አገልግሎት ሽፋኑ የሚፈለገው ደረጃ አለመድረሱና ደረጃውን የጠበቀና አለም አቀፍ ተቀባይነት ያለው የእንስሳት ኳራንታይን ጣቢያ አለመኖሩ፣ ለቁም እንስሳት ንግድ ላይ ለተሰማሩ የንግድ ተዋንያን የሚደረገው የፋይናንስ አቅርቦት በቂ አለመሆኑ፣ የቁም እንስሳት የውጭ ገበያ ትስስር በሚፈለገው ደረጃ አለመሆኑ ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡

የንግድ ሚኒስቴር ከቁም እንስሳት ግብይቱ ጋር የተያያዙ ችግሮችን በመሰረታዊነት ለመፍታት እና የቁም እንስሳት ግብይትን ዘመናዊ፣ በወቅታዊ መረጃ የተደገፈ፣ ቀልጣፋ እና ወጪ ቆጣቢ በማድረግ አርቢው፣ ህጋዊ የግብይት ተዋንያኑን፣ ሸማቹ እና ሀገሪቱ ከግብይቱ ተጠቃሚ እንዲሆኑ ለማስቻል የቁም እንስሳት ግብይት አዋጅ 819/2006 በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ፀድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡ አዋጁንም ማስፈፀም እንዲቻል የቁም እንስሳት ግብይት ደንብ ቁጥር 341//2007 እንዲሁም መመሪያ ቁጥር 004/2007 ፀድቆ ተግባራዊ እየተደረገ ይገኛል፡፡

በመሆኑም የግብይት ህግ ማዕቀፎቹን በማስፈፀም ሂደት በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳትን አያያዝ፣ አስተዳደር እንዲሁም አወጋገድ በተመለከተ ግለፅና ወጥነት ያለው አሰራር እንዲኖር ለማስቻል እንዲሁም የቁም እንስሳት ግብይት በባህሪው ከሌሎች የግብርና ምርቶች የተለየ እና ህይወት ያላቸው በመሆናቸው የመመገብ፣ የውሀ ማጠጣት እና ልዩ የጤና እንክብካቤ የሚያስፈልጋቸው በመሆኑ ይህን ዝርዝር ማንዋል ማውጣት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ ይህ ማንዋል ተዘጋጅቷል፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2
Ministry of Trade

ዓላማ

በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳትን አያያዝ፣ አስተዳደር እንዲሁም አወጋገድ ስርዓት በማስቀመጥ ወጥ የሆነ አፈጻጸም እንዲኖር በማድረግ ህገ ወጥ ንግዱን መቀነስ ህጋዊ ንግዱን ለማበረታታት ነው፡፡

## ክፍል አንድ

### 1.በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳት ማቆያ

- በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት በሽያጭ እስከሚተላለፉ ድረስ የሚቆዩበት የማቆያ ስፍራ በክልሎች/ ከተማ አስተዳደር፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ የእንስሳት ግብይቱን በሚመሩ/ በሚያስተዳድሩ አካላት ይቋቋማል፡፡
- ጊዜያዊ የቁም እንስሳት ማቆያዎቹን በማቋቋም ሂደት የከተማ አስተዳደር ማዘጋጃ ቤቶች፣ የደንብ ማስከበር ፅ/ቤቶች፣ ከግብርና ጽ/ቤቶች እንዲሁም ከሌሎች ከሚመለከታቸው አካላት ጋር በጋራ ይሰራል፡፡
- ጊዜያዊ የቁም እንስሳት ማቆያዎቹ ሲቋቋሙ የህገወጥ የቁም እንስሳት ዝውውሩን አቅጣጫና ፍሰት፣ ለቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት ያላቸው ቀረቤታ፣ መኖና ውሃ አቅርቦት፣ ለፀጥታ አጠባበቅ እንዲሁም በአጠቃላይ የቁም እንስሳት ግብይት የህግ ማዕቀፎች በሚደነግጉት መሰረት በህግ አፈፃፀሙ ሂደት የቁም እንስሳቱ ሳይጎዱ በተገቢው ሁኔታ አቆይቶ በሽያጭ ለማስተላለፍ የሚያስፈልጉ ቅድመ ሁኔታዎችን ከግምት ማስገባት ይኖርበታል፡፡
- በቋሚነት ከሚቋቋሙ ማቆያዎች በተጨማሪ ንግድን የሚያስተዳድሩ አካለት የዩኒየን ማድለቢያዎችን፣ የግለሰብ ማድለቢያዎችን፣ የግብይት ማዕከላትን፣ እንዲሁም ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ፡፡
- የግብይት አገልግሎት በማይሰጥባቸው ማቆያዎች እንዲቆዩ የሚደረጉ እንስሳት በአቅራቢያው የግብይት ማዕከላት ከሌሉ እዚያው ሽያጩን መፈጸም የሚቻል ሲሆን በአቅራቢያው የግብይት ማዕከል ካሉ ግን ወደ ግብይት ማእከላቱ በመጓጓዝ ሽያጩ መፈጸም አለበት፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 3

- የእንስሳት ማቆያው በመንግስት ባለቤትነት የተያዘ ከሆነ የመደበኛ ተግባሩን በማይቃረን ሁኔታ ታይቶ ለሌሎች ተግባሮች ህጋዊ በሆነ የኪራይ ውል መሰረት ማከራየት የሚቻል ሲሆን የሚገኘው ገቢም ማቆያ ጣቢያውን ለማጠናከርና ተያያዥ ወጪዎችን ለመሸፈን እንዲውል ይደረጋል፣
- ክልሎች/ ከተማ አስተዳድሮች፣ ዞን ወረዳና ቀበሌዎች በህገወጥ ዝውውርና ኮንትሮባንድ የሚያዙ የቁም እንስሳትን ለማቆየት የሚጠቀሙባቸው ቋሚ የእንስሳት ማቆያዎች፣ የዩኒየን ማድለቢያዎች፣ የግለሰብ ማደለቢያዎች እና የግብይት አገልግሎት የማይሰጡ እንዲሁም ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎች የሚከተሉትን መሰረተ ልማቶች ማሟላት ይኖርባቸዋል፡-

  ሀ/ በአካባቢ ቁሳቁስ የተሰራ አጥር፣

  ለ/ ለውሃ አቅርቦት ያለው አመቺነት፣

  ሐ/ ለመኖ አቅርቦት ያለው አመቺነት፣

  መ/ ለጥበቃ ያለው አመቺነት፣

## 2.ህገወጥ የቁም እንስሳት አያያዝና ርክክብ ስርዓት

- በቁም እንስሳት ግብይት የህግ ማዕቀፎች መሠረት የቁም እንስሳት የሽኝት/ የጉዞ ደረሰኝ፣ የእንስሳት ጤና ማረጋገጫ ሰርተፊኬት፣ ህጋዊ የግብይት ደረሰኝ፣ ህጋዊ ንግድ ፍቃድ ኮፒ ሳይዝ፣ ከቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ውጭ ግብይት ሲፈፀም ወይም የሽኝት/ የጉዞ ደረሰኝ ከሚጠቅሰው አቅጣጫ ውጭ ሲጓጓዝ የተገኘ የቁም እንስሳት በቁጥጥር ስር እንዲወሉ ይደረጋል፡፡
- የቁም እንስሳቱ በፌደራል ፖሊስ ወይም በገቢዎችና ጉምሩክ ባለስልጣን ወይም በንግድ ቢሮዎች፣ ኬላ ተቆጣጣሪዎች ወይም በሌላ አካል የተያዙ ከሆነ እንስሳቱን በአቅራቢያ ለሚገኙ የቁም እንስሳት ንግድን ለሚመሩ የክልል/ ከተማ አስተዳደር፣ የዞን፣ የወረዳ ወይም የቀበሌ ፅ/ቤት ያስረክባል፡፡

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. 1
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 1

* የቁም እንስሳቱ የተያዙት በክልል/ ከተማ አስተዳደር፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ ፀጥታ/ ሚሊሻ አባላት ከሆነ እንደአግባቡ የቁም እንስሳት ንግዱን ለሚመራው የክልል/ ከተማ አስተዳደር፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ ያስረክባሉ፡፡
* በህገ ወጥ መንገድ የሃገሪቱን ድንበር ተሻግረው ሲወጡ የሚያዙ የቁም እንስሳት ግን በጉምሩክ ህጉ መሠረት የሚስተናገዱ ይሆናል፡፡
* ህገ ወጥ ድርጊቱ የተፈጸመው የሚያስፈለጉ ሰነዶች ተሟልተው በሌሎች ሁኔታዎች /ከግብይት ማዕከል ውጭ በመገበያየት፣እንዲገበያይ ካልተፈቀደለት አካል ጋር በመገበያየት/ እና መሰሎች ከሆነ ህገ ወጥ ነጋዴው /ድርጅቱ/ ሰነዶችን በሙሉ እንስሳቱ በቁጥጥር ስር እንዲውሉ ላደረገው አካል ከእንስሳቱ ጋር አብሮ እንዲያስረክብ ይደረጋል፣
* እንስሳቱን የያዙት የፌደራልም ይሁን የክልል/ ከተማ አስተዳደር፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ ፀጥታ አካላት የያዙትን የቁም እንስሳትን ወደ ተዘጋጁ የቁም እንስሳት ማቆያ ጣቢያዎች በበቂ ፀጥታ አካል አጅቦ ማድረስ ይኖርባቸዋል፡፡ የቁም እንስሳት ማቆያ ጣቢያዎች እንስሳቱ ከተያዙበት አካባቢ የራቀ ከሆነ እና ርቀቱ በመንግስት ሰራተኞች የአበል አከፋፈል መመሪያ መሰረት አበል የሚያስከፍል ከሆነ አበል እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡ ክፍያውም የተያዙ እንስሳትን ለማስተዳደር በክልሉ/ ከተማ አስተዳደሩ ከሚመደበው ተዘዋዋሪ በጀት/ ሪቮልቪንግ ፈንድ/ የሚከፈል ሆኖ ለክፍያ የወጣው ወጪ ከእንስሳቱ ሽያጭ ተቀናሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡
* የቁም እንስሳቱ የተያዙት በተሽከርካሪ ሲጓጓዙ ከሆነ ተሽከርካሪው የቁም እንስሳቱን ወደ ማቆያው ጣቢያ እንዲያደረስ ይደረጋል፡፡ የቁም እንስሳቱ የተያዙት በእግር ሲነዱ ከሆነና ማቆያው በቅርብ የሚገኝ ከሆነ የቁም እንስሳቱ ባለቤቶች ነድተው እንዲያደርሱ የሚደረግ ሲሆን ማቆያው የራቀ ከሆነ በተሽከርካሪ እንዲጓጓዙ ተደርጎ ወጪው የቁም እንስሳቱን ለማቆየት ከሚወጣው ወጪ ጋር ታሳቢ ተደርጎ ከእንስሳቱ ሽያጭ የሚሸፈን ይሆናል፡፡
* የቁም እንስሳቱን የያዙት አካላት የቁም እንስሳቱን ወደ ማቆያ ጣቢያው ካደረሱ በኋላ ማቆያውን ከሚያስተዳድረው አካል እንዲሁም በአካባቢው የቁም እንስሳት ንግድን ከሚመራው አካል ርክክቡን በተመለከተ ሀላፊነት የተሰጠው ወይም የተወከሉ አካለት በተገኙበት የእንስሳቱን ርክክብ ይፈፅማል፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 7

- ርክክቡ የሚፈፀመው የርክክብ ቅፅን መሰረት ባደረገ መልኩ ሲሆን የርክክቡ ቅፁ የቁም እንስሳቱ የተያዙበትን ምክንያት፣ የቁም እንስሳቱን ብዛት፣ ዓይነት፣ የተነሱበትንና የተያዙበትን ቦታ፣ ቀን ሰዓት፣ የባለንብረቱ ስም፣ እንስሳቱን የጫነው የመኪናው ዓይነትና የሰሌዳ/ ታርጋ ቁጥር፣ የሾፌር ስም፣ የማቆያው ልዩ ስም፣ አካባቢ/ ቦታ፣ የተረካቢ ስም፣ የቁም እንስሳት ንግድን ከሚመራው አካል የተወከሉ ግለሰቦች ስም እንዲሁም ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን የያዘ መሆን ይገባዋል (የርክክቡ ቅፁ ከማንዋሉ ጋር አብሮ ተያይዟል)።
- የርክክቡ ቅፁ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ ኦርጅናሉ ለባለንብረቱ ወይንም ለሹፌሩ፣ አንዱ ኮፒ ለእንስሳቱ ማቆያ ሀላፊ/ ለተረካቢ፣ ቀሪው ኮፒ የቁም እንስሳት ንግድን ከሚመራው አካል የተወከሉ ግለሰቦች/ አረካካቢው ይሰጣል።
- የቁም እንስሳቱ ከተያዙ በኋላ የሚቀርቡ መረጃዎችን ለመለየት እንዲቻል የቁም እንስሳቱ ባለንብረት ወይንም ሹፌሩ የቁም እንስሳቱ የተያዙበትን ምክንያት (የጎደሉ መረጃዎችን) አምኖ በርክክቡ ቅፅ ላይ እንዲፈርም ይደረጋል።
- የቁም እንስሳቱ ማቆያው በሚቆዩበት ወቅት በሌላ እንስሳት እንዳይቀየሩ የቁም እንስሳቱ ወደ ማቆያው በሚገቡበት ወቅት ማቆያውን በሚያስተዳድረው እና በአካባቢው የቁም እንስሳት ንግድን በሚመራው አካል የሚታወቅ ልዩ ምልክት (በማርከር፣ በቀለም፣ ታግ፣ በመሳሰሉት) ይደረጋል። ለዚህም የሚመለከተው አካል አስፈላጊ ቅድመ ዝግጅቶችን ያደርጋል።

## ክፍል ሁለት

### 3.በህገወጥ ዝውውርና ኮንትሮባንድ ንግድ የሚያዙ የቁም እንስሳት አስተዳደር

- በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳት በሽያጭ እስኪወገዱ ድረስ ክልሎች/ ከተማ አስተዳድሮች፣ ዞን፣ ወረዳና ቀበሌዎች በሚያዘጋጁት ቋሚ የእንስሳት ማቆያ ወይም የዩኒየን/ ግለሰብ ማድለቢያ፣ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል ወይም ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎችን ይጠቀማሉ።



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation

ሀ. ቋሚ የእንስሳት ማቆያ ጣቢያዎች አስተዳደር

- ክልሎች/ ከተማ አስተዳድሮች፣ ዞን ወረዳና ቀበሌዎች በህገወጥ ዝውውርና ኮንትሮባንድ የሚያዙ የቁም እንስሳትን ለማቆየት ቋሚ የእንስሳት ማቆያ ያዘጋጁ ከሆነ አስተዳደሩን በተመለከተ ራሳቸው ቋሚ አደረጃጀት ፈጥረው ሊያስተዳደሩ ወይም በአነስተኛና ጥቃቅን ለተደራጁ ወይም ለዩኒየኖች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡
- የእንስሳት ማቆያ ጣቢያ ማስተዳደሩን በራሳቸው ለመምራት ከወሰኑ ካላቸው የንግድ መዋቅር በቋሚነት ወይም በተደራቢነት የማቆያውን የእለትተለት እንቅስቃሴ የሚከታተል አካል መሰየም አለበት፡፡ በተጨማሪም እንስሳት በሚያዙበት ወቅት እንስሳቱን የሚንከባከቡ እንስሳት ተንከባካቢዎችን በቋሚነት ወይም በኮንትራት ቀጥሮ መመደብ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የተያዙ የቁም እንስሳቱ በሽያጭ እስኪወገዱ ድረስ በማቆያ በሚቆዩበት ወቅት ለመኖ፣ ውሃ፣ ህክምና፣ ለጥበቃ፣ ለእንስሳት ተንከባካቢና ለሌሎች ወጪዎች የሚውል ቋሚ ተዘዋዋሪ (ሪቮልቪንግ) በጀት መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡
- እንስሳቱን ለማቆየት የሚወጡ ወጪዎች (የመኖ፣ ውሃ፣ ህክምና፣ ጥበቃ ወ.ዘ.ተ ግዢዎች) የመንግስትን የዕቃና አገልግሎት ግዢ መመሪያ መከተል የሚገባው ሲሆን በአስፈላጊው ሰነድ ተደግፈው እንስሳቱ ከተሸጡ በኂላ የወጣው ወጪ ከእንስሳቱ ሽያጭ ላይ ተቀንሶ ወደ በጀቱ ይተካል፡፡ ቀሪው ገንዘብ እንደ አግባቡ እንስሳቱ በጠቆማ የተያዙ ከሆነ ለጠቋሚ (40%) የሚከፈል ሲሆን ቀሪው ለክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ ገቢ ይሆናል፣ በፖሊስ የተያዘ ከሆነ በመመሪያው መሠረት ለጽ/ቤቱ ገቢ ይሆናል፡፡
- በአንፃሩ የማቆያውን አስተዳደር ለአነስተኛና ጥቃቅን ለተደራጁ ወይም ለዩኒየኖች የሚሰጡ ከሆነ የንግድ ቢሮዎችና ፅ/ቤቶቹ በማቆያው የሚቆዩ የቁም እንስሳትን አስተዳደርን በተመለከተ ከአነስተኛና ጥቃቅን ተቋማቱ ወይም ከዩኒየኖች ጋር ዝርዝር ውል አዘጋጅቶ መፈራረም ይገባቸዋል፡፡ ውሉ ዝርዝር ጉዳዮችን ማካተት የሚገባው ሲሆን፡- የቁም እንስሳቱን በማቆየት ሂደት በቀን ለአንድ እንስሳት የሚጠይቀው ክፍያ በእንስሳት ዓይነት (በግ፣ ፍየል፣ ግመል፣ ከብት)፣ በቆይታ ሂደት የሚጎዱና የሚሞቱ የቁም እንስሳትን በተመለከተ፣ የማቆያውን ንብረት አጠቃቀም እንዲሁም ሌሎች

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2
Ministry of Trade Archives

ጉዳዮችን በዝርዝር መያዝ ይገባዋል። (መነሻ ውል ከዚህ ማንዋል ጋር የተያያዘ ሲሆን የንግድ ፅ/ቤቶች ከራሳቸው ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ሊያሻሽሉት ይችላሉ)

- ተቋማቱ (ጥቃቅንና አነስተኛ ወይም ዩኒየኖች) የካፒታል ችግር ያለባቸው ከሆነ የንግድ ቢሮ ወይንም ፅ/ቤቱ ለእንስሳቱ ማቆያ የሚውል ቋሚ ተተካኪ (ሪቮልቪንግ) በጀት በማዘጋጀት በቅድመ ክፍያ ወይም በብድር መልክ ሊያቀርቡ ይችላሉ። እንስሳቱ ከተሸጡ በኋላ የወጣው ወጪ ከእንስሳቱ ሽያጭ ላይ ተቀንሶ ወደ በጀቱ (ብድሩ) የሚተካ ሲሆን በውሉ መሰረት ለተቋማቱ (ጥቃቅንና አነስተኛ ወይም ዩኒየኖች) የሚከፈለው ክፍያ ይፈጸማል።
- የተያዙት የቁም እንስሳት ሳይሸጡ በማቆያው እያሉ ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ ውሳኔ ከተሰጠ የቁም እንስሳቱ ባለቤቶች የቁም እንሳቱን ለማቆየት የወጣውን ወጪ ለክልሎች/ ከተማ አስተዳድሮች፣ ለዞን ወረዳና ቀበሌዎች ወይም ለዩኒየኑ፣ ለግለሰብ ማደለቢያው፣ ለግብይት ማዕከላቱ ወይም ለቁም እንስሳት ማቆያነት ለዋሉት ማቆያዎች ከፍለው የቁም እንስሳቱን ይረከባሉ።

## ለ. ጊዜያዊ የቁም እንስሳት ማቆያ ጣቢያዎች /የዩኒየን፣ ግለሰብ ማድለቢያ፣ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል እና ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎች/ አስተዳደር

- ከላይ እንደተገለፀው ክልሎች/ ከተማ አስተዳድሮች፣ ዞን ወረዳና ቀበሌዎች በህገወጥ ዝውውርና ኮንትሮባንድ የሚያዙ የቁም እንስሳትን ለማቆየት የዩኒየን ማድለቢያዎች፣ የግለሰብ ማድለቢያዎች፣ የግብይት ማዕከላት፣ እንዲሁም ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎችን ሊጠቀሙ ይችላሉ።
- የቁም እንስሳት ግብይቱን የሚመራው የንግድ መዋቅር በህገወጥ ዝውውርና ኮንትሮባንድ የሚያዙ የቁም እንስሳትን ለማቆየት የዩኒየን ማድለቢያዎች፣ የግለሰብ ማድለቢያዎች፣ የግብይት ማዕከላት እንዲሁም ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል የሚችሉ ማቆያዎችን በመጠቀም ሂደት መሰረተ ልማቱን (ማቆያውን) ብቻ በመከራየት የተያዙትን የቁም እንስሳት አስተዳደር በራሳቸው መምራት ወይም የመሰረተ ልማቱንም (ማቆያውን) ሆነ የተያዙትን የቁም እንስሳት አስተዳደሩን ሙሉ ለሙሉ አገልግሎት ሊገዙ ይችላሉ።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2
Ministry of Trade

- መሰረተ ልማቱን (ማቆያውን) ብቻ በመከራየት የተያዙትን የቁም እንስሳት አስተዳደር በራሳቸው የሚመሩ ከሆነ ካላቸው የንግድ መዋቅር በቋሚነት ወይም በተደራቢነት የማቆያውን የእለት ተዕለት እንቅስቃሴ የሚከታተል አካል መሰየም አለበት፡፡
- በተጨማሪም የቁም እንስሳት በሚያዙበት ወቅት እንስሳቱን የሚንከባከቡ እንስሳት ተንከባካቢዎችን በቋሚነት ወይም በኮንትራት ቀጥሮ መመደብ አለባቸው፡፡ በተጨማሪም የተያዙ የቁም እንስሳቱ በሽያጭ እስኪወገዱ ድረስ በማቆያ በሚቆዩበት ወቅት ለመኖ፣ ውሃ፣ ህክምና፣ ለጥበቃ፣ ለእንስሳት ተንከባካቢና ለሌሎች ወጪዎች የሚውል ቋሚ ተዘዋዋሪ (ሪቮልቪንግ) በጀት መመደብ ይኖርባቸዋል፡፡
- የመሰረተ ልማቱን (ማቆያውን) ኪራይ በተመለከተ ዝርዝር የኪራይ ውል መዘጋጀት የሚገባው ሲሆን ክፍያው በቅድሚያ ወይም የቁም እንስሳቱ ከተሸጡ በኃላ ሊከፈል ይችላል፡፡
- የቁም እንስሳቱን ለማቆየት የወጡ ወጪዎች በሰነድ መደገፍ የሚገባቸው ሲሆን እንስሳቱ ከተሸጡ በኂላ የመሰረተ ልማቱን (ማቆያውን) ኪራይ ጨምሮ ሌሎች የወጡ ወጪዎች ከእንስሳቱ ሽያጭ ላይ ተቀንሶ ወደ በጀቱ ይተካል፡፡ ቀሪው ገንዘብ እንደ አግባቡ እንስሳቱ በጥቆማ የተያዙ ከሆነ ለጠቋሚ (40%) የሚከፈል ሲሆን ቀሪው ለክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ ገቢ ይሆናል፣ በፖሊስ የተያዘ ከሆነ በመመሪያው መሠረት ለፅ/ቤቱ ገቢ ይሆናል፡፡
- በሌላ በኩል የቁም እንስሳት ግብይት መዋቅሩ (የክልል/ ከተማ አስተዳደር፣ ዞን፣ ወረዳ፣ ቀበሌ) የመሰረተ ልማቱንም (ማቆያውን) ሆነ የተያዙትን የቁም እንስሳት አስተዳደር ሙሉ ለሙሉ ለዩኒየን ማድለቢያዎች፣ የግለሰብ ማደለቢያዎች፣ የግብይት ማዕከላት፣ የሚሰጥ ከሆነ አንድን የቁም እንስሳን ለአንድ ቀን ለማቆየት የሚያስፈልገውን ወጪ (የመኖ፣ የውሃ፣ የጥበቃ፣ የማቆያውን ኪራይና ሌሎች ወጪዎቹን ያካተተ) መሰረት በማድረግ ዝርዝር ውል በማዘጋጀት ከአገልግሎት ሰጪ ተቋሙ (ማድለቢያዎች፣ የግብይት ማዕከላት፣ እንዲሁም ሌሎች ለቁም እንስሳት ማቆያነት መዋል ከሚችሉ ማቆያዎች) ጋር ይፈራረማል፡፡
- ውሉ ለየአንዳንዱ የቁም እንስሳት ዓይነት (የዳልጋ ከብት፣ በግና ፍየል፣ ግመል) በቀን የሚከፈለውን ክፍያ፣ የሚመገበውን የመኖ ዓይነት፣ በቁም እንስሳቱ ላይ ለሚደረስ

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

ችግር ተጠያቂነትን በተመለከተ እንዲሁም አጠቃላይ የቁም እንስሳቱን ሳይጎዱ ለሽያጭ ለማቅረብ የሚያስፈልጉ ጉዳዮችን ያካተተ መሆን ይገባዋል።

- ውሉ የቁም እንስሳቱ ከመያዛቸው በፊት መዘጋጀት እና መፈርም የሚገባው ሲሆን ዋጋውን በተመለከተ ግን የወቅቱን ዋጋ መሰረት ባደረገ መልኩ የቁም እንስሳቱ ተይዘው ወደ ማቆያው ሲገቡ የሚወሰን ይሆናል።
- ውል የሚገቡ ማቆያ ጣቢያዎችን ለመለየት ጨረታ በማውጣት ወይንም እንደ አካባቢው የማቆያ ጣቢያዎች ብዛትና ተጨባጭ ሁኔታ በድርድር ሊካሄድ ይችላል። በተጨማሪም የመረጣው ሒደት ከላይ በማንዋሉ ማቆያጣቢያ ሊያሟሏቸው የሚገበው መስፈርቶችን መሰረት ያደረገ መሆን ይገባዋል።
- የቁም እንስሳቱን በአንድ ጊዜ ሙሉ ለሙሉ መሸጥ የማይቻልበት ሁኔታ ስለሚኖር አገልግሎት ሰጪው አንዱን የቁም እንስሳት ለማቆየት በተስማማበት ዋጋ የቁም እንስሳቱ ተሸጠው እስከሚያልቁ ድረስ አገልግሎት የመስጠት ግዴታ እንዳለበት ውሉ ላይ መካተት ይገባዋል።
- የተያዙት የቁም እንስሳት ሳይሸጡ በማቆያው እያሉ ለባለቤቶቹ እንዲመለሱ ውሳኔ ከተሰጠ የቁም እንስሳቱ ባለቤቶች የቁም እንሳቱን ለማቆየት የወጣውን ወጪ በውሉ ላይ በተጠቀሰው ዋጋ መሰረት ለዩኒየኑ፣ ለግለሰብ ማደለቢያው፣ ለግብይት ማዕከላቱ፣ ወይም ለቁም እንስሳት ማቆያነት ለዋሉት ማቆያዎች ከፍለው የቁም እንስሳቱን እንዲረከቡ ይደረጋል።
- የቁም እንስሳት ማቆያ ማስተዳደሩን እና የማቆያውን ንብረት አጠቃቀም (መነሻ ውል/ለተቋማቱ (ጥቃቅንና አነስተኛ ወይም ዩኒየኖች)በህገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ተየይዘው በመንግስት ማቆያ ውስጥ ላሉ ለቁም እንስሳት አገልግሎት ከሚሰጡ አካላት ጋር የኮንትራት ውል ስምምነት ቅፅ፣በህገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ለለተያዙ ለቁም እንስሳት ማቆያ ከሚያከራዩ አካላት ጋር የሚደረግ የኮንትራት ውል ስምምነት ቅፅ ተያይዟል።

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2
Ministry of Trade Archives

# ክፍል ሶስት

## 4. አወጋገድ/ሽያጭ ሂደት

- የቁም እንስሳቱን የያዘው የክልሎች/ከተማ አስተዳድሮች፣ የዞን ወረዳና የቀበሌ የግብይት መዋቅር በቁም እንስሳት ግብይት አዋጁ አንቀፅ 15 ንዑስ አንቀፅ 8 በተገለፀው መሰረት በሕገ ወጥ መንገድ ሲጓጓዙ ወይም ግብይት ሲፈጸምባቸው የተገኙ የቁም እንስሳትን እንደ አግባቡ በመጀመሪያ ወይም በሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል አቅርቦ ይሸጣል፡፡
- የቁም እንስሳቱ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ከሆነ ሙሉ ለሙሉ በአከባቢው ወደሚገኝ የመጀመሪያ ወይም ሁለተኛ ደረጃ የቁም እንስሳት ግብይት ማዕከል አቅርቦ ይሸጣል፡፡ እንደ ግብይት ማዕከላቱ የርቀትና የብዛት ሁኔታ የቁም እንስሳቱን በእግር ወይም በተሽከርካሪ እንዲጓጓዙ የሚደረግ ሲሆን ለቁም እንስሳት ነጂዎች ወይም ለተሽከርካሪዎች የቁም እንስሳቱን ለማቆየት ከተያዘው በጀት ላይ እንዲከፈል በማድረግ ከቁም እንስሳት ሽያጩ ተቀናሽ የሚደረግ ይሆናል፡፡
- የቁም እንስሳቱ ከፍተኛ ቁጥር ካላቸው የቁም እንስሳት ግብይት አዋጁ አንቀፅ 10 ንዑስ አንቀፅ 2) ‹ለ› እንዲሁም በቁም እንስሳት ግብይት ደንቡ አንቀፅ 11 ንዑስ አንቀፅ 2 በሚያስቀምጠው መሰረት ሁሉንም የቁም እንስሳት ወደ ግብይት ማዕከላት ማምጣት ሳያስፈልግ የቁም እንስሳቱን ናሙና ወይም ኤሌክትሮኒክስ ማስረጃ በማቅረብ ግብይት ከተፈፀመ በኃላ ርክክቡን በማቆያው ጣቢያ ማድረግ ይችላል፡፡
- በግብይት ማዕከሉ የሽያጩን ሂደት የሚከታተልና የሚቆጣጠር እንዲሁም ሽያጩን የሚያስፈጽም እና የሽያጩን ገንዘብ የሚሰበስብ ከግብይት መዋቅር ቢሮ ወይም ጽ/ቤት የተወከለ ኮሚቴ በቦታው መገኘት ይኖርበታል፡፡
- የቁም እንስሳቱ ብዛት ከፍተኛ ከሆነ እንስሳቱን በተለያየ ደረጃ (መደብ) በመመደብ ሽያጩን ማካሄድ ይቻላል፡፡ ሆኖም የቁም እንስሳቱን በጥቅል ለመግዛት ፍላጎት ያላቸው በቂ የቁም እንስሳት ገገርዎች ካሉና ሁኔታው ይህን የሚፈቅድ ከሆነ ቅድሚያ ማግኘት ይችላሉ፡፡ የቁም እንስሳቱ አነስተኛ ቁጥር ያለቸው ከሆነ ወይም በተለያየ ደረጃ (መደብ) ለመመደብ አዳጋች ከሆነ እያንዳንዱን የቁም እንስሳት በተናጠል መሸጥ ይገባል፡፡



Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

- የግብይት መዋቅሩ የቁም እንስሳቱን በግብይት ማዕከላቱ በመሸጥና ገንዘብ በመሰብሰብ ሂደት ፀጥታ የሚያስጠብቁ የፀጥታ አካላት እንዲገኙ ማድረግ ይኖርበታል።
- የቁም እንስሳቱ ከላይ በተገለፀው አግባብ መሸጥ ካልተቻለ ወይም በዚህ አግባብ ለመሸጥ ሁኔታው አመቺ ካልሆነ በቁም እንስሳት ግብይት ደንቡ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 ‹ለ› ላይ በተገለፀው መሰረት በጊዜያዊ ማቆያው ውስጥ በግልጽ ጨረታ ወይም በግልጽ ጨረታ ካልተሸጠ ለመንግስት ወይም ለግል ተቋማት በድርድር እንዲሸጥ ይደረጋል።
- የቁም እንስሳቱ በጨረታ የሚሸጡ ከሆነ በጨረታው ላይ ከፍተኛ ቁጥር ያለው ተሳታፊ እንዲኖርና የቁም እንስሳቱን በተሻለ ዋጋ መሸጥ እንዲቻል ከጨረታው ቀን በፊት በመገናኛ ብዙሃን እና በማስታወቂያ በቁም እንስሳት ግብይት ማዕከላት፣ የቁም እንስሳት ላኪዎችና ማድለቢያ ጣቢያዎች በሚገኙበት ፣በሉካንዳ፣ ሆቴልና ሬስቶራንቶች እንዲሁም የቁም እንስሳት ሊገዙ የሚችሉ ተቋማትና ግለሰቦች በብዛት በሚገኙበት ቦታዎች ሁሉ መለጠፍ ይገባዋል። በተጨማሪም በአካባቢው ለሚገኙ ዋናዋና የቁም እንስሳት ነጋዴዎች ጥሪ እንዲደርሳቸው ይደረጋል።
- በጨረታው ግለሰቦች መሳተፍ የሚችሉ ሲሆን ከሸማች፤ከኅብረት ስራ ማህበር እና ከአርብቶ አደር በስተቀር የቁም እንስሳትን የሚገዙ ከሆኑ ግን የንግድ ፈቃድ ኮፒ ይዘው መገኘት ይኖርባቸዋል።
- የቁም እንስሳቱ ብዛት ከፍተኛ ከሆነ እንስሳቱን በተለያየ ደረጃ (መደብ) በመመደብ ጨረታውን ማካሄድ ይቻላል። ሆኖም የቁም እንስሳቱን በጥቅል ለመጫረት ፍላጎት ያላቸው በቂ ተጫራቶች ካሉ ቅድሚያ ማግኘት ይችላሉ። የቁም እንስሳቱ አነስተኛ ቁጥር ያላቸው ከሆነ ወይም በተለያየ ደረጃ (መደብ) ለመመደብ አዳጋች ከሆነ እያንዳንዱን የቁም እንስሳት በተናጠል ማጫረት ይገባል።
- ተጫራቾች ከጨረታው በፊት ተመጣጣኝ የጨረታ ማስከበሪያ ከጨረታው በፊት በ የግብይት መዋቅሩ ወይም ጨረታውን በሚያካሂደው አካል ስም በ C.P.O ወይም በካሽ ማስያዝ ይኖርባቸዋል ሲሆን በካሽ የሚያሲዙ ከሆነ አጫራቹ አካል ደረሰኝ ይሰጣል። ተጫራቾች ለጨረታው ያስያዙት ገንዘብ በጨረታው ለተሸነፉ ወዲያውኑ የሚመለስላቸው ሲሆን ለአሸናፊዎች ግን ከአሸነፉት የቁም እንስሳት ዋጋ ጋር አብሮ የሚታሰብ ይሆናል።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

- የጨረታው አሸናፊ በጨረታው ያሸነፈውን የቁም እንስሳት ክፍያ ሙሉ ለሙሉ በ ተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፍሎ መረከብ ይገባዋል። በተሰጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ከፍሎ እንስሳቱን ካልተረከበ ያስያዘው ገንዘብ ለግብይት መዋቅሩ ገቢ ተደርጎ ጨረታው እንደገና ይካሄዳል።
- የግብይት መዋቅሩ በማቆያው የጨረታውን ሂደት ፀጥታ የሚያስጠብቁ የፀጥታ አካላት እንዲገኙ ማድረግ ይኖርበታል።
- የቁም እንስሳቱን ከላይ በተጠቀሰው መልኩ የግብይት ማዕከላት ወይም በጨረታ መሸጥ ካልተቻለ ወይም በዚህ መልኩ ለመሸጥ ሁኔታዎች አመቺ ካልሆነ ለመንግስት ወይም ለግል ተቋማት በድርድር እንዲሸጥ ይደረጋል።
- የግብይት መዋቅሩ የቁም እንስሳት ገበያ መረጃ ስርዓትን ፣ የቁም እንስሳት ለኤክስፖርት ቄራዎች የሚቀርብበትን እንዲሁም በግብይት ማዕከላት ያለውን የቁም እንስሳት ዋጋ ጥናት መሰረት በማድረግ ለድርድሩ መነሻ ዋጋ ይወስናል።
- የቁም እንስሳቱን በድርድር የሚገዛው ተቋም ወይም ግለሰብ የቁም እንስሳቱን በአካል በመገኘት እንዲያይ መደረግ ይኖርበታል። የድርድሩ ዋጋ በግብይት መዋቅሩ አስተባባሪነት በተውጣጣ ኮሚቴ መፅደቅ ይኖርበታል።
- የዋጋ ስምምነት ተደርጎ ከፀደቀ በኃላ የሽያጭ ውል ተዘጋጅቶ መፈራርም የሚገባ ሲሆን የቁም እንስሳቱን በማቆያው በመገኘት መረከብ ይገባዋል።
- የግብይት መዋቅሩ የቁም እንስሳቱን በግብይት ማዕከላትም ሆነ ፣ በጨረታ ወይም በድርድር ሲሸጥ ለገገርው አካል ህጋዊ ደረሰኝ ወይም አግባብነት ያለው ሰነድ መስጠት ይገባዋል።
- የተያዙት የቁም እንስሳት ከሽያጩ በፊት በሰው ፣በእንስሳትና በአካባቢው ላይ ጉዳት የሚያስከትል መሆኑ በእንስሳት ሀኪም ከተረጋገጠ በእንስሳት ሀኪሙ በሚመከረው የማስወገጃ መንገድ መሰረት እንዲወገዱ ይደረጋል።
- የጨረታው አሸናፊ ተለይቶ ከአቅም በላይና አሳማኝ በሆነ ምክንያት እንስሳቱ በማቆያው የሚቀዩበት ሁኔታ ካለ እና ከግብይት መዋቅሩ ወይም ከማቆያው ጣቢያ ባለቤቶች ፍቃድ ካገኘ አሸናፊነቱ ከታወቀበት ጊዜ ጀምሮ ለቁም እንስሳቱ የሚወጡ ልዩ ልዩ ወጪዎች በሙሉ በጨረታ አሸናፊው የሚሸፈኑ ይሆናሉ።

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 2

## 5.የሽያጭ ገንዘብ አስተዳደር

- የቁም እንስሳቱ በግብይት ማዕከል የተሸጡ ከሆነ ግብይቱ በጥሬ ገንዘብ ስለሚሆን የቁም እንስሳቱን ማቆያ አስተዳደሩን ሙሉ ለሙሉ የግብይት መዋቅሩ ወሰዶ ከነበር ከሽያጩ ላይ ለመኖ፣ለውሃ፣ለሌሎች ወጪዎች የወጣው ወጪ በሰነዱ መሰረት ተቀናሽ ተደርጎ ወደ ተዘዋዋሪ በጀት (ሪቮልቪንግ) እንዲገባ ተደርጎ ቀሪው ገንዘብ የግብይት መዋቅሩ ባዘጋጀው ዝግ የሂሳብ ቁጥር ገቢ ይደረጋል፡፡ የግብይት መዋቅሩ የማቆያ ቦታ አዘጋጅቶ የቁም እንስሳቱን አስተዳደር ግን በኮንትራት ለጥቃቅንና አነስተኛ ወይም ለሌላ አካል ሰጥቶ ከነበር ለዚህ አካል የሚከፈለው ክፍያ በተጨማሪ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
- አንድን የቁም እንስሳት ለአንድ ቀን ለማቆየት የሚከፈለውን ክፍያ መሰረት ባደረገ መልኩ በሚደረግ የውል ስምምነት ማቆያውን ጨምሮ አስተዳደሩን ሙሉ ለሙሉ ለዩኒየን፣ ለግለሰብ ፣ ለግብርና ምርምር ማዕከላት ወይንም ለሌላ አካል ተሰጠቶ ከነበር በውሉ መሰረት ክፍያው ከቁም እንስሳቱ ሽያጭ ላይ እንዲከፈል ተደርጎ ቀሪው ገንዘብ የግብይት መዋቅሩ ባዘጋጀው ዝግ አካውንት ገቢ ይደረጋል ፡፡
- የተያዙት የቁም እንስሳት የተሸጡት በጨረታ ወይም በድርድር ከሆነ ገዢው አካል ሙሉ ክፍያውን በግብይት መዋቅሩ የባንክ ሂሳብ ቁጥር ገቢ በማድረግ በሚያቀርበው የገቢ ደረሰኝ መሰረት የቁም እንስሳቱን ይረከባል፡፡ በዚህ መሰረት የግብይት መዋቅሩ የቁም እንስሳቱን ማቆያ አስተዳደር ሙሉ ለሙሉ የግብይት መዋቅሩ ወሰዶ ከነበር ወደ ግብይት መዋቅሩ የሂሳብ ቁጥር ላይ ገቢ ከተደረገው የሽያጭ ገንዘብ ላይ ለመኖ፣ለውሃ፣ለሌሎች ወጪዎች የወጣው ወጪ በሰነዱ መሰረት ተቀናሽ ተደርጎ ወደ ተዘዋዋሪ በጀቱ (ሪቮልቪንግ ፈንድ ) እንዲገባ የሚያደርግ ሲሆን ማቆያውን ጨምሩ አስተዳደሩን ሙሉ ለሙሉ ለዩንየን፣ ለግለሰብ ፣ ለግብርና ምርምር ማዕከላት ወይንም ለሌላ አካል ተሰጠቶ ከነበር በውሉ መሰረት ክፍያው ወደ ግብይት መዋቅሩ የሂሳብ ቁጥር ላይ ገቢ ከተደረገው የቁም እንስሳቱ ሽያጭ ገንዘብ ላይ እንዲከፈል ተደርጎ ቀሪው ገንዘብ የግብይት መዋቅሩ ወዳዘጋጀው ዝግ አካውንት እንዲዞር ይደረጋል ፡፡
- የቁም እንስሳቱ ሽያጭ ገንዘብ በቁም እንስሳት ግብይት ደንቡ አንቀፅ 19 ንዑስ አንቀፅ 3 ፣ 4 እና 5 በተደነገገው መሰረት በፍትህ አካል ውሳኔ እስኪሰጥ ድረስ ገንዘቡ በዝግ የባንክ ሂሳብ ይቀመጣል፡፡



የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን ቤተ መዛግብትና ዶክመንቴሽን ቁ. ፫
Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 3
Ministry of Trade Archives

- የቁም እንስሳቱ የተያዘበት ግለሰብ በየደረጃው አግባብነት ላለው አካልና ፍርደቤት አቅርቦ የቁም እንስሳቱ ህገወጥነት ተረጋግጦ የመጨረሻ ውሳኔ ከፀና ወይንም መሰረት በተወሰነው የጊዜ ገደብ ውስጥ ይግባኝ ያላቀረበ ከሆነና የቁም እንስሳቱ የተያዙት በጥቆማ ከሆነ ለቁም እንስሳቱ ሽያጭ የወጣው ወጪ ተቀንሶ በዝግ የሂሳብ ቁጥር ከተቀመጠው የቁም እንስሳቱ ሽያጭ ላይ 40% ለጠቋሚው ወይም ያለጥቆማ የተያዘ ከሆነ ለያዘው የመንግሥት ፀጥታ ተቋም ይከፈላል፤ ቀሪው 60% ለክልሉ ወይም ከተማ አስተዳደሩ ገቢ ይሆናል፣ በፖሊስ የተያዘ ከሆነ በመመሪያው መሠረት ለፅ/ቤቱ ገቢ ይሆናል፡፡
- በየደረጃው ያለ አግባብነት ያለው አካል (የግብይት መዋቅር) ወይንም ፍርድ ቤት የቁም እንስሳቱን ህገወጥነት ከሻረው የቁም እንስሳውን ለመሸጥ የወጣው ወጪ ተቀናሽ ተደርጎ በዝግ የሂሳብ ቁጥር የተቀመጠው የቁም እንስሳቱ ሽያጭ ገንዘብ ለባለቤቱ ተመላሽ ይደረጋል፡፡

## ክፍል አራት

### 6.በጊዚያዊ የቁም እንስሳት ማቆያ የሚሞቱ እንስሳትን በተመለከተ

- በጊዜያዊ የቁም እንስሳት ማቆያ ከተያዙት የቁም እንስሳት መካከል ከአያያዝ ችግር ለሚከሰት የእንስሳት ሞት እንስሳቱን ለማስተዳደር ሀላፊነት የወሰደው አካል ተጠያቂ ሲሆን የአሟሟቱ ሁኔታ በተመለከተ በአካባቢው ባሉ የእንስሳት ሀኪሞች እንዲረጋገጥ ይደረጋል፡፡
- የሞተውን የቁም እንስሳት ዋጋ በተመለከተ የግብይት መዋቅሩ የወቅቱን የቁም እንስሳት መሰረት በማድረግ በመወሰን ለማስተዳደር የወሰደው አካል እንዲከፍል ወይንም ከሚያገኘው የአገልግሎት ክፍያ ላይ ተቀናሽ ይደረጋል፡፡
- ከተያዙት እንስሳት ውስጥ በተለያዩ አጋጣሚዎች በሚከሰቱ የእንስሳት ድንገተኛ ሞት ሲያጋጥም ያገቹ ክፍልበአቅራቢያው ካለው የእንስሳት ጤና ጥበቃ ክፍል የእንስሳውን

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 3
Ministry of Trade Archives

ሞት ምክንያት የሚያረጋግጥ ህጋዊ የምስክር ወረቀት በመያዝ ይህንንም የሞት የምስክር ወረቀት በመያዝ በአቅራቢያ ለሚገኘው የፀጥታ አካል ማሳወቅ አለበት፡፡

- በተጨማሪም የቁም እንስሳትን ድንገተኛ ሞት በተመለከተ የሞቱትን እንስሳ በድን በአግባቡ ማስወገድ አለበት፡፡
- ያገርው ከላይ በዝርዝር የቀረቡትን መረጃዎች በተጠናቀረ መልኩ ካቀረበ ቀደም ሲል ተረክቦ ለጎደሉት እንስሳት ተጠያቂ አይሆንም፡፡

## 7.ህገወጥ የቁም እንስሳትን የጫነ ተሽከርካሪ፤አሽከርካሪ እና የቁም እንስሳት ባለቤት በተመለከተ

- በቁም እንስሳት ግብይት አዋጁ አንቀፅ 17 ንዑስ አንቀፅ 10 መሰረት ህገ ወጥ ግብይት የተፈፀመባቸው የቁም እንስሳትን ያጓጓዘ ማንኛውም አጓጓዥ ከሁለት ዓመት በማይበልጥ ቀላል እስራት እና ከብር 30,000 በማይበልጥ መቀጮ ይቀጣል፡፡
- በመሆኑም ህገወጥ ግብይት የተፈፀመባቸው ወይንም በህገ ወጥ መንገድ የሚጓጓዙ የ የቁም እንስሳትን የጫነ ተሽከርካሪ የቁም እንስሳቱን በማቆያው ጣቢያ ካራገፈ በኃላ ተሽከርካሪው በማቆያው ጣቢያ ወይንም በግብይት መዋቅሩ ቅጥር ግቢ ወይንም በአካባቢው በሚገኝ የፀጥታ አካል ግቢ ውስጥ ወይንም የግብይት መዋቅሩ እንዲቆይ በሚወስነውና አስተማማኝ ጥበቃ ባለበት ቦታ እንዲቆይ ያደርጋል፡፡

## 9.የክትትልና የግምገማ ስርዓት

- በክልሎች/ከተማ አስተዳድሮች፣ በዞን ወረዳና ቀበሌ የሚገኙ የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት ትግበራ ግብረሐይል ህገወጥ ግብይት የተፈፀመባቸው እና በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት አያያዝ ፣ አስተዳደርና አወጋገድ አፈፃፀምን እንዲሁም አጠቃላይ የቁም እንስሳት ግብይት ስርዓት ዝርጋታው አፈፃፀም በመገምገም የሚታዩ ክፍተቶችን ያርማል፡፡
- ክልሎች/ከተማ አስተዳድሮች፣ ዞን ወረዳና ቀበሌ የሚገኙ የግብይት መዋቅሮች ህገወጥ ግብይት የተፈፀመባቸው እና በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት አያያዝ ፣ አስተዳደርና አወጋገድ አፈፃፀምን እንዲሁም አጠቃላይ የቁም እንስሳት

የኢትዮጵያ ገቢዎችና ጉምሩክ ባለሥልጣን
Ethiopian Revenues and Customs Authority
Ministry of Trade Archives

ግብይት ስርዓት ዝርጋታው አፈፃፀምን በተመለከተ ችግሮች ሲገጥማቸው ከንግድ ሚኒስቴር ጋር በመወያየት እንዲፈታ ይደረጋል።

- ህገወጥ ግብይት የተፈፀመባቸው እና በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የሚያዙ የቁም እንስሳት አያያዝ ፣ አስተዳደርና አወጋገድን በተመለከተ በዚህ ማንዋል ያልተሸፈኑ ልዩ ጉዳዮች ሲገጥሙ በሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች ወጥ በሆነ መልኩ ለመተግበር እንዲቻል ጉዳዮቹ ለንግድ ሚኒስቴር ቀርበው ንግድ ሚኒስቴር ማብራሪያውን ወይም አሰራሩን በሰርኩላር መልክ ለሁሉም ክልሎችና ከተማ አስተዳደሮች እንዲልክ ይደረጋል።

## 10.የተለያዩ ቅፃቅፆች

ቅጽ 1

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ንግድ ሚኒስቴር

ሴሪ ቁጥር ------------------

ቀን ----------------

**በህገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ለሚያዙ የቁም እንስሳት የመረካከቢያ ቅጽ**

1. የቁም እንስሳቱ ዓይነትና ብዛት፤-
   1.1. የዳልጋ ከብት ብዛት ፤ --------------,
   1.2. የበግ ብዛት ፤----------------,
   1.3. የፍየል ብዛት ፤--------------,
   1.4. የግመል ብዛት ፤-------------,
   1.5. ሌሎች ፤--------------
2. የቁም እንስሳቱ በህገወጥነት የተያዙበት ምክንያት፤- ----------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------------
3. የቁም እንስሳቱ
   3.1. ለጉዞ የተነሱበት ቦታ ------------
   3.2. ሲንቀሳቀሱ የተያዙበትን ቦታ/ ከተማ፣ --------------------- ቀበሌ ----------------------
   3.3. የተያዙበት ቀን --------------- ሰዓት፣---------
4. የቁም እንስሳቱ ባለንብረት ስም፣ -------------------------------
5. የቁም እንስሳቱን የጫነው
   5.1. የመኪናው ዓይነት ----------------------
   5.2. የሰሌዳ/ ታርጋ ቁጥር፣ ------------------
   5.3. የሾፌር ስም፣ ---------------------------
   5.4 የመንጃ ፈቃድ ቁጥር--------------------
6. የማቆያው ቦታው 6.1. ልዩ ስም፣ --------------
   6.2. ያለበት ክልል---------- ዞን (ከተማ)-------- ወረዳ ----- ቀበሌ ስም፣--------

Ministry of Trade Archives

ቅጽ 2

# በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ንግድ ሚኒስቴር

ሴሪ ቁጥር -----------------

ቀን --------------

## ከማቆያው ጣቢያ ለሚወጡ ( በሽያጭ/ ለባለቤቱ ሲመለሱ) የቁም እንስሳት የመረካከቢያ ቅጽ

1. የቁም እንስሳቱ ዓይነትና ብዛት፤-
    1.1. የዳልጋ ከብት ብዛት ፤ --------------,
    1.2. የበግ ብዛት፤---------------------------,
    1.3. የፍየል ብዛት፤-----------------------,
    1.4. የግመል ብዛት፤-----------------------,
    1.5. ሌላ ብዛት፤----------------------------
2. የቁም እንስሳቱ የተወገዱበት ዘዴ፤-
    2.1 በጨረታ --------------------
    2.2 በድርድር -------------------
    2.3 በሌላ ካለ ይጠቀስ ----------
3. የቁም እንስሳቱ
    3.1 የተሸጡበት ገበያ ማዕከል ስም --------------------------------
    3.2 የተሸጡበት ቀን --------------- ሰዓት፣----------------------
4. የገገርው ግለሰብ/ ድርጅት/ተቋም/ ኅ/ስራ ማህበር ስም፣ -----------------
5. የቁም እንስሳት ርክክብ
    5.1 የቁም እንስሳት ንግድን ከሚመራው አካል እንዲያስረክብ የተወከለው ግለሰብ / የቁም እንስሳውን የተረከበው የማቆያ ጣቢያ ተወካይ ስም --------------------------------
    5.2 የመታወቂያ ቁጥር ------------------------------
    5.3 የአስረካቢው ፊርማ -----------------------------
    5.4 የነበሩ እማኞች
        ስም ---------------------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -------------------
        ስም ---------------------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -------------------
        ስም -------------------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -------------------
6. የቁም እንስሳቱ የተሸጡበት ዋጋ እና ሌሎች አስፈላጊ መረጃዎችን -----------------------------------------------
---------------------------------------------------------------------------------------------------------------
---------------------------------------------------------------------------------------------------
7. ከ ----------------------------------- ክልል/ ከተማ አስተዳደር/ ዞን/ ወረዳ/ የቁም እንስሳት ንግድን ከሚመራው አካል ከላይ የተጠቀሱትን የቁም እንስሳት ተቀብያለሁ።

ማሳሰቢያ፡-

1.ይህ ደረሰኝ የቁም እንስሳትን በመያዝ ወደ ማቆያ ጣቢያዎች ለማስረከብ ስለሚረዳ የተያዘባቸውም ሆነ የያዘው አካል ለመረጃነት ስለሚጠቅማቸው መረጃውን መያዝ ይገባቸዋል።

2.ይህ ደረሰኝ በሶስት ኮፒ ተዘጋጅቶ የመጀመሪያው (ዋናው ነጩ) የቁም እንስሳቱ ለተያዘበት ግለሰብ ወይም የመኪናው ሰሌዳ ጎን ቁጥር እየተጻፈበት ለመኪናው ሾፌር፤ ሁለተኛው (ሮዝ ) የቁም እንስሳቱን ለሚረከበው የማቆያ ጣቢያው ተረካቢ ሶስተኛው ኮፒ በክልል ንግድን ለሚቆጣጠረው ቢሮ (ሰማያዊው)በጥራዙ ላይ እንዳለ ለቁጥጥር ይቀመጣል።

ቅጽ 4

## በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ንግድ ሚኒስቴር

ሴሪ ቁጥር ------------------

ቀን ------------------

**በህገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ለለተያዙ ለቁም እንስሳት ማቆያ ከሚያከራዩ አካላት ጋር የሚደረግ የኮንትራት ውል ስምምነት ቅፅ**

1. ባለንብረት/ድርጅት ስም፣ ------------------------------------
2. የቁም እንስሳት ማቆያው የሚገኝበት ቦታ:-ልዩ ስም፣-------------- ክልል----------- ዞን/ክ/ከተማ/-------ወረዳ ---- ከተማ------------- ቀበሌ --------
3. የማቆያው :-
   3.1 ዓይነት ------------------
   3.2 ስፋት --------------------
   3.3 በውስጡ ያሉ መሰረተ ልማቶች -----------------------
4. የውል ሰጭ ግዴታ
   4.1 ከውል ተቀባዩ ጋር በገቡት ስምምነት መሰረት ለእንስሳቱ ማቆያነት ለተከራየው የማቆያ ጣቢያ ኪራይ እንስሳቱ በሚሸጡበት ጊዜ ሙሉ በሙሉ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
   4.2 እንስሳቱ በማቆያ ጣቢያ በቆይታቸው ግዜ ለሚያደርሱት የመሰረተ ልማት ጉዳቶች ለማስጠገን ባለማቆያው የሚያወጣውን ወጭ በሚቀርበው ህጋዊ ደረሰኝ መሰረት የመተካት ግዴታ አለበት፡፡
5. የውል ተቀባይ ግዴታ
   5.1. ከውል ሰጭ ጋር በገቡት ስምምነት መሰረት የእንስሳት ማቆያ የማቅረብ ግዴታ አለበት፡፡
   5.2. ለእንስሳት ማቆያው አጥር እና በውስጡ ላሉ የመሰረተ ልማቶች በወቀቱ ተከታትሎ አስፈላጊውን ጥገና የማድረግ ግዴታ አለበት፡፡
   5.3. ከላይ በተጠቀሰው መሰረት ውል ተቀባይ ለ ውል ሰጭ በህገወጥ መንገድ ሲጓጓዙ የተያዙ የቁም እንስሳት ማቆያነት የሚያገለግለውን የቁም እንስሳት ማቆያ ጣቢያ ኪራይ የውለታው ጊዜ ማብቂያ ድረስ በቀን ለአንድ እንስሳ በእንስሳው አይነት የሚከፈል የአገልግሎት ክፍያ ታስቦ በድምሩ በቀን------ብር እንዲከፈለኝ መስማማቴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡ እኔም ውል ሰጭ ከላይ በተዘረዘሩት ነጥቦች መሰረት የተስማማሁ መሆኔን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ ፡፡
   5.4. ውሉን ሳያከብር የተገኘ ወገን የውሉን 30 %/ፐርሰንት / ለመንግስት ተቀጥቶ ውሉ እንዲጸና ይደረጋል፡፡

6. **የውል ሰጭ**

ስም -------------------------------------

ፊርማ -------------------------------------

ቀን -------------------------------------

**የውል ተቀባይ**

ስም -------------------------------------

ፊርማ -------------------------------------

ቀን -------------------------------------

7. **የነበሩ እማኞች**

ስም ------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -----------------

ስም ------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -----------------

ስም ------------------------- ፊርማ ----------------- ቀን -----------------

Ethiopian Revenues and Customs Authority
Records & Documentation No. 3
Ministry of Trade

ቅጽ 5

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት ንግድ ሚኒስቴር

ሴሪ ቁጥር ------------------

ቀን ------------------

በህገወጥ መንገድ ሲንቀሳቀሱ ተይዘው ላሉ የቁም እንስሳት የማቆያ ጣቢያ ኪራይ እና አገልግሎት ከሚሰጡ አካላት ጋር የኮንትራት መግቢያ ውል ስምምነት ቅፅ

1. **የውል ሰጪ :-**
   1.1 ተቋም ስም---------ክልል-----ዞን(ክ/ከተማ)--------ወረዳ----------ከተማ----------ቀበሌ--------
2. **የውል ተቀባይ :-**
   2.1 ስም------ ክልል-----ዞን (ክ/ከተማ)--------ወረዳ----------ከተማ----------ቀበሌ--------
   ባለንብረት/ድርጅት/ስም፣ ------------------------------------
3. የቁም እንስሳት ማቆያው የሚገኝበት ቦታ፡-ልዩ ስም፣------------------------------ ክልል---------
   ዞን/ክ/ከተማ/------ ወረዳ ---- ከተማ------ ቀበሌ ------
4. **የእንስሳት ማቆያው :-**
   4.1 ዓይነት ------------------------------------------------------
   4.2 ስፋት ------------------------------------------------------
   4.3 በውስጡ ያሉ መሰረተ ልማቶች ------------------------
5. **አገልግሎቱ የሚሰጠው የቁም እንስሳቱ ዓይነት** ፡-
   5.1 የዳልጋ ከብት፤ ----------------,
   5.2 የበግ ፤-----------------------,
   5.3 የፍየል ፤--------------------,
   5.4 የግመል ፤------------------,
   5.5 ሌላ ብዛት ፤------------------
6. **የውል አይነት**

   6.1 የእንስሳት ማቆያ ጣቢያ ኪራይ

   6.2. በማቆያ ውስጥ ላሉ እንስሳት

   6.2.1 የህክምና
   6.2.2 በቂ መኖና ውሃ
   6.2.3 የጥበቃ እና
   6.2.4 ሌሎች አገልግሎት ማቅረብና መስጠት
7. **የውል ሰጭ ግዴታ**
   7.1 ከውል ተቀባዩ ጋር በገቡት ስምምነት መሰረት እንስሳቱ በሚሸጡበት ጊዜ ለእንስሳቱ ማቆያነት ስተከራየው የማቆያ ጣቢያ ኪራይ እና እንስሳቱን ለማቆየት፤ለመንከባከብ፤ ያወጣቸውን ወጪ ሙሉ በሙሉ የመክፈል ግዴታ አለበት፡፡
   7.2. ከአቅም በላይ የሆነ የጸጥታ ችግር በሚያጋጥምበት ጊዜ አስፈላጊውን ድጋፍና ትብብረ የማድረግ ግዴታ አለበት ፡፡

Ethiopian Revenues and Customs Authority Records & Documentation No. 2

